**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ወቅት: የ2020 ዓ.ም. የክረምት ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 022284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א.<u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב.<u>የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና አራት ምዕራፎችን ይዟል።

ከእያንዳንዱ ምዕራፍ <u>አንድ</u> ጥያቄ መልስ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (1x25) | — | 25 | ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (1x25) | — | 25 | ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | — | (1x25) | — | 25 | ነጥብ |
| ምዕራፍ አራት | — | (1x25) | — | 25 | ነጥብ |
| | | በአጠቃላይ | — | 100 | ነጥብ |

**<u>ልብ በል</u>፦ ተስማሚ ፈተና** (מבחן מותאם) **የተፈቀደለት** ተማሪ <u>ሦስት</u> ጥያቄዎችን ይመልስ፦ ከምዕራፍ አንድ **<u>ወይም</u>** ከምዕራፍ ሁለት አንድ ጥያቄ፣ ከምዕራፍ ሦስት አንድ ጥያቄ እና ከምዕራፍ አራት አንድ ጥያቄ።

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

<u>በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ</u> ጻፍ። ለማሰቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት። ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ማሰቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ቅሉ ለሴትም ለወንድም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תש"ף, 2020

**מספר השאלון: 022284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה ארבעה פרקים.

ענה על שאלה <u>אחת</u> מכל פרק.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שני | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שלישי | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק רביעי | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| | | סה"כ | — | 100 נקודות |

<u>**שים לב:**</u> תלמיד **שאושר לו מבחן מותאם** יענה על <u>שלוש</u> שאלות: שאלה אחת מפרק ראשון **<u>או</u>** מפרק שני, שאלה אחת מפרק שלישי ושאלה אחת מפרק רביעי.

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>. רשוֹם "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.
כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (25 ነጥብ)

### የመጀመሪያው ወቅት፦ ብሔርተኝነት በእስራኤልና በሕዝቦች ዘንድ — ከጅማሬው እስከ 1920

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**1. ብሔርተኝነት (לאומיות)**

ኦ. በአውሮፓ ውስጥ ለብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች መለምለም የኢንዱስትሪው አብዮት (ኢንደስትሪያሊዝም) ያደረገውን ተጽዕኖ አብራራ እና ለመለምለማቸው መንስዔ የሆነውን ተጨማሪ ምክንያት አቅርብ። (12 ነጥብ)

ᗷ. ለአንድ ብሔር ሰዎች የጋራ መለያ የሆኑት ምን ምን ናቸው?

ብሔርተኝነት በአውሮፓ ማኅበረሰብ ላይ ወይም በፖለቲካው ካርታ ላይ ያደረገውን አንድ ለውጥ አቅርብ። (13 ነጥብ)

**2. የጽዮናውያን እንቅስቃሴ**

ኦ. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ለጽዮናውያን እንቅስቃሴ ማቆጥቆጥ ምክንያት የሆኑትን ሦስት መንስኤዎች አብራራ። (12 ነጥብ)

ᗷ. ሔርጼል "የይሁዳውያን ሀገር" በሚለው መጽሐፉ ላይ ለ"ይሁዳውያን ችግር" ያቀረበውን መፍትሔ አብራራ።
ሔርጼል ይህን መፍትሔ እንዳያራምድ እንቅፋት ከሆኑት ችግሮች ውስጥ ሁለቱን አሳይ።
(13 ነጥብ)

**3. ምድረ እስራኤል ከ1882–1914 ባሉት ዓመታት**

ኦ. በዚህ ወቅት በምድረ እስራኤል ላይ የተመሠረቱትን ሠፈራዎች ሁለት መለያዎች አብራራ።
ሃባሮን ሮችልድ ለሠፈራዎች የሰጠውን ዕርዳታ አንድ ጥቅም/ቅድሚያ እና አንድ ችግር/ጉድለት አቅርብ። (13 ነጥብ)

ᗷ. "השומר"/"ሃሾሜር" የሚባለውን ድርጅት ለማቋቋም ምክንያት ከሆኑት ሁለቱን አሳይ እና ከእንቅስቃሴዎቹ ሁለቱን አቅርብ። (12 ነጥብ)

ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል ▶

## ምዕራፍ ሁለት (25 ነጥብ)

### ሁለተኛው ወቅት፦ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል (ከ1920-1939)፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የይሁዳውያን ሠፈራ በምድረ እስራኤል

ከ4-6 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**4. አንደኛው የዓለም ጦርነት — ማስረጃዎች/ሰነዶች እና ለውጦች**

ሀ. "የዊልሶን 14 ነጥቦች" ማስረጃ/ሰነድ ይፋ መውጣት ዓላማ ምን ነበር? ይህን ዓላማ ለማራመድ ከተዘጋጀው ማስረጃ ውስጥ አንድ ንዑስ አንቀጽ አቅርብ። (15 ነጥብ)

ለ. ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓው ፖለቲካዊ ካርታ ላይ የተካሄዱትን ሁለት ለውጦች አቅርብ። (10 ነጥብ)

**5. በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የይሁዳዊያን ሠፈራ በምድረ እስራኤል**

ሀ. በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል ወደ እስራኤል አገር ለመምጣት (עלייה) ምክንያት ከሆኑት ሁለቱን አብራራ።

የዚህን ወቅት አዲስ ገቢዎች ሁለት መለያዎች አቅርብ።
(13 ነጥብ)

ለ. በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሃያዎቹ እና ሠላሳዎቹ ዓመታት ውስጥ የይሁዳውያን ሠፈራ የነበሩትን ሁለት ስኬቶች አቅርብ፦ በግብርናው ሠፈራ መስክ/ዘርፍ አንድ ስኬት እና በከተማው ሠፈራ መስክ/ዘርፍ አንድ ስኬት። (12 ነጥብ)

**6. በአሥራ ዘጠኝ ሠላሳዎቹ ዓመታት ይሁዳዊያን፣ ዓረቦች እና ብሪታንያዊያን በእስራኤል ሀገር**

ሀ. የ"ዐረቦች አመጽ" ("המרד הערבי") ምንድን ነው?

ለዚህ የ"ዐረቦች አመጽ" ምላሽ የይሁዳውያን ሠፈራ እንቅስቃሴ ያደረገባቸውን ሁለት መንገዶች አቅርብ።
(13 ነጥብ)

ለ. የሦስተኛውን "ነጩን መጽሐፍ" ይዘት አቅርብ እና የይሁዳውያን ሠፈራን በተመለከተ የብሪታንያ መመሪያ መቀየሩ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል ▶

## ምዕራፍ ሦስት (25 ነጥብ)

### ሦስተኛው ወቅት፦ አምባገነኑ መንግሥት (המשטר הטוטליטרי)፣ ናዚነት፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የይሁዳውያን መጨፍጨፍ (השואה)

ከ7-10 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**7. የናዚዎች መንግሥት በጀርመን ከ1933-1934 ባሉት ዓመታት (המשטר הנאצי בגרמניה בשנים 1933-1938)**

**ኦ.** ከ1933-1934 ባሉት ዓመታት ውስጥ ሂትለር የናዚን መንግስት ለማጠናከር ያደረጋቸውን ሁለት ድርጊቶች አሳይ።
ካቀረብካቸው ድርጊቶች አንዱ እንዴት የናዚን ሥልጣን እንዳጠናከረ አብራራ።
(13 ነጥብ)

**ኀ.** የኒርንበርግን ሕግ (1935) ይዘት አሳይና በእነዚህ ሕጎች ውስጥ አንድ የናዚ ርዕዮተዓለም መመሪያ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ። (12 ነጥብ)

**8. ማጎሪያዎቹ (הגטאות)**

**ኦ.** ናዚዎቹ ማጎሪያዎቹን በማቋቋም የነበራቸውን ሁለት ዓላማዎች አብራራ እና ማጎሪያዎቹን የተቆጣጠሩባቸውን ሁለት መንገዶች አቅርብ። (13 ነጥብ)

**ኀ.** የዮድርናቶችን አባላት አንድ ማመንታት (המלדיד) አብራራ። (12 ነጥብ)

**9. የወጣቶች እንቅስቃሴ፣ እርዳታና ነብስ አድን (תנועות הנוער, סיוע והצלה)**

**ኦ.** የ"መጨረሻው መፍትሔ" ከመተግበሩ በፊት የማጎሪያው የወጣቶች እንቅስቃሴ ያደረጋቸውን ሁለት ድርጊቶች አቅርብ እና በወጣቶች እንቅስቃሴ መሳተፉ አባላት ለሆኑት በማጎሪያው (ጌቶዎቹ) ያለውን ሕይወት ለመቋቋም እንዴት እንዳገዛቸው አብራራ። (12 ነጥብ)

**ኀ.** በናዚዎች በተወረሩ አገራት ያሉ ይሁዳውያን ያልሆኑ የአካባቢው ኗሪዎች ይሁዳዊያንን ለመርዳት ያነሳሳቸውን መንስኤ አብራራ እና በዚህ ድርጊት ክንዋኔ ከነበሩባቸው ችግሮች ውስጥ ሁለቱን አሳይ። (13 ነጥብ)

**10. ማጎሪያዎቹ "በመጨረሻው መፍትሔ" ጊዜ**

**ኦ.** ናዚዎች ሕዝበ እስራኤልን ለመደምሰስ ዓላማ ማድረጋቸውን በማጎሪያው ውስጥ የነበሩት ይሁዳዊያን ለምን ለመረዳት ተቸገሩ? ሁለት ምክንያቶችን አቅርብ።
(15 ነጥብ)

**ኀ.** በማጎሪያዎቹ (በጌቶዎች) የነበረውን አመጽ ያቀናበሩት እነማን ነበሩ፣ ዓላማዎቻቸውስ ምን ምን ነበሩ?
(10 ነጥብ)

ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል ▶

## ምዕራፍ አራት (25 ነጥብ)

## አራተኛው ወቅት፦ እስራኤል ሀገርን በመካከለኛው ምስራቅ መገንባት

ከ11-14 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> መልስ።

**11.** <u>**የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ**</u>

**ሀ.** በአሜሪካንና በሶቭዬት ኅብረት መካከል ሽኩቻ ቢኖርም እንኳን፣ በኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተላለፈውን የተባበሩት መንግሥታትን ድርጅት ውሳኔ ለምን ሁለቱም እንደደገፉት አብራራ። (11 ነጥብ)

**ለ.** በኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተላለፈውን የተባበሩት መንግሥታትን ድርጅት ዋነኛ ውሳኔ አብራራ።
በዚህ ውሳኔ ላይ የነበረው የይሁዳውያን ምላሽ ምን ነበር? እንዲሁም የዐረቦች ምላሽ ምን ነበር? (14 ነጥብ)

**12.** <u>**በአሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ እና ስልሳዎቹ ዓመታት ወደ እስራኤል ሀገር መግባት (היילע) እና መስተንግዶ**</u>

**ሀ.** ሀገሪቱ ከተቋቋመች በኋላ ወዲያውኑ በትልቁ የአዲስ ገቢዎች መስተንግዶ ላይ እስራኤል ሀገር ከነበሩባት ችግሮች <u>ሁለቱን</u> አብራራ። (13 ነጥብ)

**ለ.** በዚህን ጊዜ የመጡት አዲስ ገቢዎች ለእስራኤል ሀገር ከሚከተሉት መስኮች <u>በሁለቱ</u>፦ በሠፈራ፣ በዲሞግራፊ እና በባሕል ያበረከቱትን አስተዋጽዖ አቅርብ። (12 ነጥብ)

**13.** <u>**የ"ሾአ" ትውስታ (זיכרון השואה)**</u>

**ሀ.** በአሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹ ዓመታት የእስራኤል ማኅበረሰብ ከ"ሾአ" ለተረፉት የነበራቸውን አመለካከት አሳይ እና ለዚህ አመለካከት መንስኤ ከሆኑት <u>አንዱን</u> ጥቀስ። (12 ነጥብ)

**ለ.** እስራኤል ሀገር የ"ሾአ"ን መታሰቢያ ጥበቃ ለማድረግ የሄደችባቸውን <u>ሁለት</u> መንገዶች አቅርብ፣ እና የዚህ የ"ሾአ" መታሰቢያ ያለውን አስፈላጊነት አብራራ። (13 ነጥብ)

**14.** <u>**የስድስቱ ቀን ጦርነት/የአስተሰርዮ ጦርነት (מלחמת ששת הימים / מלחמת יום הכיפורים)**</u>

ከነዚህ ጦርነቶች ውስጥ <u>አንዱን</u> ምረጥ፦ የስድስቱ ቀን ጦርነት (1967) <u>ወይም</u> የአስተሰርዮ ጦርነት (1973)።

**ሀ.** ለመረጥከው ጦርነት መፈንዳት መንስኤ ከሆኑት ውስጥ <u>ሁለቱን</u> አብራራ። (12 ነጥብ)

**ለ.** የመረጥከውን ጦርነት ቅጽበታዊ ውጤቶች አሳይና እነዚህ ውጤቶች በጦርነቱ ምክንያት በእስራኤል ማኅበረሰብ በተነቃቁት ስሜቶች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረጉ አብራራ። (13 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך